# ክቡር ፕሬዝደንት ይቅር ብለናል ግን...

(ከአብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል)

(ይህ ጽሑፍ በቅጽ 13 ቁጥር 772፣ ጥቅምት 22 ቀን 2007 ዓ.ም በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ታትሟል፡፡ ጋዜጣውን የማያገኙ ቢያነቡት ይጠቅማል በሚል መንፈስ በዚህ ድረ-ገጽ በኩል እንዲቀርብ ተልኳል፡፡)

የኢፌዴሪ ፕሬዝደንት ክቡር ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ ለሕዝብ ተወካዮች እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ንግግር በማድረግ የዓመቱን የሕግ አወጣጥ መርሐ-ግብር (Legislative Program) ማሳወቃቸው ይታወሳል፡፡ የዘንድሮው የፕሬዝደንቱ ንግግር ለየት ያለ ሃሳብ የተካተተበት መሆኑን አስተውያለሁ፡፡ ይኸውም፤ ክቡር ፕሬዝዳንቱ በኢህአዴግ የሃያ አራት ዓመት የአስተዳደር ዘመን ተገልፆ የማያውቅ ቃል መናገራቸውን አድምጫለሁ፡፡

ላለፉት ሃያ አራት ዓመታት እንዳየነው ኢህአዴግ በታሪኩ በርዕሰ ብሔር ደረጃ ቀርቶ በተራ ካድሬ ደረጃ ሕዝብን በይፋ ይቅርታ ጠይቆ አያውቅም፡፡ ዘንድሮ ግን የመብራት መቆራረጥን በተመለከተ በክቡር ፕሬዝዳንቱ ንግግር ውስጥ በማካተት በይፋ ይቅርታ ጠይቋል፡፡

ኢህአዴግ ይህንን ያደረገው "ካንጀት" ይሁን "ካንገት" ባይታወቅም፤ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አሊያም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለተፈጸመ ስህተት ይቅርታ መጠየቅ የስልጡንነት ምልክት እንጂ፣ በበኩሌ ሽንፈትንም ድክመትንም የሚያሳይ ሆኖ አይታየኝም፡፡ መሳሳትም ሆነ ድክመት በኢህአዴግ የተጀመረ ይመስል ኢህአዴግ ይህንን ቃል ለዘመናት ለምን ሲፈራውና ሲሸሸው እንደኖረ ግን ከቶም ሊገባኝ ያልቻለ ጉዳይ ነው፡፡ እነሆ! ዘንድሮ ይህንን እንደ መርግ የከበደ ቃል ከሀገሪቱ የመጀመሪያው ሰው (ከርዕሰ ብሔሩ) አንደበት ሰምተናል፡፡ እናም ይህንኑ ቃል መነሻ በማድረግ ይህቺን ማስታወሻ ለክቡር ፕሬዝዳንቱ ይድረስ ማለትን መረጥሁ፡፡

ክቡር ፕሬዝደንት! የማይሳሳት የማይሰራ ብቻ ነው፡፡ እናም ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት እኔና ቤተሰቤ መንግስትዎን (መንግስታችንን) በይፋ ይቅር ብለናል፡፡ ይቅር ያልነው ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስታችንን ፈርተንና ተሸማቀን ሳይሆን፤ ይቅርታ መጠየቅ የጀመረው ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስታችን ይቅርታ መጠየቅ የሚያሳፍር መስሎት "ተሸማቆ" ይቅርታ መጠየቅ እንዳያቆም ለማደፋፈር በማሰብ ነው፡፡

ክቡር ፕሬዝደንት! የእርስዎን ፕሬዝዳንታዊ ንግግር ካዳመጥን በኋላ "እውነት የመብራት መቆራረጥ ብቻ ነው እንዴ ይቅርታ ሊጠየቅበት የሚገባው ጉዳይ?" የሚለውን ጥያቄ እኔና ቤተሰቤ አንስተን ተወያይተናል፡፡ እናም፤ ለቀረበው የይቅርታ ጥያቄ "ይቅር" ብንልም ይቅርታ ሊጠየቅበት የሚገባው ጉዳይ ግን "የመብራት መቆራረጥ" ብቻ አለመሆኑን በታላቅ አክብሮት ልንገልጽልዎ እንወዳለን፡፡ የእኛ ይቅርታ እርስዎ ለዜጎች እንደሚያደርጉት ይቅርታና ምህረት "ፍትህ ሚኒስቴር ይየው፣ መንግሥት ያቅርበው፣ ምናምን..." ማለት ስለማያስፈልገው በእኛ

በኩል ይቅርታ ላልቀረበባቸውም ጉዳዮች ሁሉ ይቅር ብለናል፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ የእኛን ፈለግ ተከትሎ ይቅር እንደሚልም ተስፋ እናደርጋለን፡፡

ክቡር ፕሬዝደንት! "ይቅርታ ሊጠየቅበት የሚገባው ጉዳይ የመብራት መቆራረጥ ብቻ አደለም" የምንለው ከመሬት ተነስተን አደለም፡፡ ይህንን ለማስረገጥ በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የእርስዎንም የዚህን ጋዜጣ አንባቢዎችንም ጊዜ ላለማባከን ከመብራት፣ ከውሃና ከትራንስፖርት ጋር የተያያዙ ጥቂት ማሳያዎችን ብቻ አነሳለሁ፡፡

እኔና ቤተሰቤ የምንኖረው በኦሮሚያ ክልል፣ ፊንፊኔ ዙሪያ ዞን፣ ለገዳዲ - ለገጣፎ ከተማ ነው፡፡ የለገዳዲ - ለገጣፎ ከተማ ከአዲስ አበባ (ፊንፊኔ) ጋር ያለው ቅርበት የዓይንና የአፍንጫን ያህል ነው፡፡ በሁለቱ ከተሞች መካከል ያለው ድንበር የጣሊያኗን ሮም እና የቫቲካን ሲቲን እስኪመስል ድረስ ተገጣጥመዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በቤት ኪራይ የተማረሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ወደ ታዳጊዋ ለገጣፎ ተሻግረው መኖር ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡

ለገጣፎ ብቻ ሳትሆን በአጠቃላይ በፊንፊኔ ዙሪያ ያሉ ከተሞች የአዲስ አበባን ችግር እያቃለሉ በመሆኑ፤ ቀደም ሲል የነበሩት የእነዚህ ከተሞች መሰረተ ልማቶች በበቂ ሁኔታ የሕዝቡን ፍላጎት መሸከም አልቻሉም፡፡ ከነዚህ የመሰረተ ልማት ችግሮች አንዱ መብራት ነው፡፡

ክቡር ፕሬዝደንት! እርስዎ በዓመታዊ ንግግርዎ የጠቀሱት "የመብራት መቆራረጥ"ን በተመለከተ ነው፡፡ የለገጣፎ-ለገዳዲ ከተማ ችግር ግን "የመቆራረጥ" ችግር ብቻ አደለም፡፡ ቀድሞ ነገር መብራት መቼ ገባልንና ነው የሚቆራረጠው ክቡር ፕሬዝደንት?! መቆራረጥ ብቻማ ቢሆን ያው እን'ዳገር እንሆን ነበር፡፡ ከአዲስ አበባም ከመብራት ኃይልም ጓሮ የምትገኘውና የአዲስ አበባን ችግር ባልጠና ጀርባዋ የተሸከመቺው የለገጣፎ-ለገዳዲ ከተማ ሰማንያ በመቶ የሚሆነው ነዋሪዋ በቤቱ የመብራት ቆጣሪ አልገባለትም፡፡

ክቡር ፕሬዝደንት! የመብራት ኅርፍ በደጃፋችን አልፎ በሰሜንም በደቡብም፣ በምስራቅም በምዕራብም ያሉ የገጠር ከተሞችን ብርሃን በብርሃን ሲያደርግ እዚሁ ፊንፊኔ ጓሮ ተቀምጠን ሰማይ ጠቀስ የመብራት ኃይል ምሰሶዎችን ተደግፈን እንቆዝማለን፡፡

በኩራዝም በፋኖስም፣ በሻማም በእንጨትም እየተጠቀምን በሰላም ከምንኖርበት ሁኔታ መብራት ኃይል "አለሁላችሁ! መብራት እንድትጠቀሙ አደርጋለሁ" አለ፡፡ ጅማሮውንም አሳየን፡፡ ይሁን እንጂ፣ አበው 'ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ' እንዲሉ፤ "ስድስት ሺህ ከተሞችን በብርሃን አጥለቀልቃለሁ" እያለ የፎከረው መብራት ኃይል ከተማችን እየሰፋች ስትመጣ የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ ማለት አበዛ፡፡

እዚህ ላይ 'ታዲያ እንዴት ሆናችሁ ነው እየኖራችሁ ያላችሁት?' የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል፡፡ በኔ የመሀይም ግምት ሰማንያ በመቶ የሚሆነው የለገዳዲ-ለገጣፎ ነዋሪ በአሁኑ ወቅት መብራት የሚያገኘው ቀደም ሲል መብራት ከገባላቸው ወንድሞችና እህቶች በቀጫጭን ገመዶች እየወሰደ ነው፡፡

አንዴ በግንድ፣ ሌላ ጊዜ በስኒ፣ ቆየት ብሎ በቆጣሪ፣… መታጣት እየተመካኘ ለገዳዲ-ለገጣፎ መብራት አሮባታል፡፡ ክቡር ፕሬዝደንት! እግር ጥሎዎት ወደ ለገጣፎ ቢመጡ በቀጫጭን አጣናዎች ምሰሶነትና በቀጫጭን ሽቦዎች አማካይነት ሁለት ሦስት ኪሎ ሜትር አቆራርጠው የሚሄዱ የመብራት ገመዶችን፤ አሊያም ከወዲያ ወዲህ፣ ከወዲህ ወዲያ እንደ ሸረሪት ድር የተዳወሩ የመብራት ገመዶችን ሊመለከቱ ይችላሉ፡፡

ይህ ብቻ አደለም! ሰሞኑን በመንደራችን ስዘዋወር ምን እንዳየሁ ያውቃሉ ክቡር ፕሬዝደንት!? መብራት በአንዲት መስመር ብቻ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ሲወሰድ ነው ያየሁት፡፡ ነገሩ ገረመኝና "ሁለተኛው መስመር የት አለ?" በማለት ጠየቅኩ፡፡ "ና ጉድ ተመልከት!" አሉና እውነትም "ጉድ" አሳዩኝ፡፡ ጫፏ ወሃ በያዘች ኩባያ ውስጥ የተነከረች አንዲት የኤሌክትሪክ ገመድ አሳዩኝ፡፡ መቼስ ኤሌክትሪክ ብርሃን የሚሰጠው በፖዘቲቭ እና በኔጋቲቭ (ማለትም በእሳትና በውሃ ይሉታል ባለሙያዎች) መስመሮች አይደል?… አዎ! እሳቱን ከጎረቤት ውሃውን ከቤት አቀናጅቶ መብራት ያገኛል የለገዳዲ-ለገጣፎ ሕዝብ፡፡ ነገሩ የጨነቀው እርጉዝ ያገባል እንዲሉ ነው፡፡ በጥንቃቄ ጉድለት ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ግን አስቡት! - በተለይ ምንም በማያውቁት ሕፃናት ላይ…!

የመብራት ነገር ከተነሳ አይቀር አንድ ነገር ልጨምር ክቡር ፕሬዝደንት! በለገጣፎ ከተማ አንዲት ቅንጣት አምፑል የመንገድ መብራት የለም፡፡ በአካባቢያችን ያን ያህል የከፋ ወሮበላ ባያስቸግረንም እኛን ብቻ ሳይሆን እኛን አልፎ አዲስ አበቤውን እያስቸገረ ያለው የጅብ መንጋ ሕፃናት ልጆቻችንን ሸክፈን ገና በአስራ ሁለት ሰዓት ቤታችን እንድንከተት እያደረገን ነው፡፡ ከመሸ በኋላ መንቀሳቀስ ችግር ነው፡፡ የአካባቢው አርሶ አደር ልጆች የማታ ትምህርት መማር አልቻሉም፡፡

በእርግጥ እነዚህ ችግሮች የአካባቢያችን መስተዳደር የሥራ ድርሻ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡ ክቡር ፕሬዝደንት! እነሱስ ቢሆኑ በበላይ አካል "እንዲህ አድርጉ" ቢባሉ ምን ይላቸዋል? ምንም አይላቸው! እንዲያውም በአንድ ሀገር የፕሬዝዳንት ወይም የንጉሥ ቃል ተሰሚነቱ የላቀ ነው፡፡

ክቡር ፕሬዝደንት! የከተማችን አመራር ከኮብል ስቶንና ከውሃ ወይም ከኮብል ስቶንና ከመንገድ መብራት ለእኛ የትኛው መቅደም እንዳለበት እንኳ ስላልገባው ውሃና መብራቱን ትቶ የኮብል ስቶን መንገድ ሲሰራና ሲመርቅ ይውላል፡፡ መስተዳድሩ እግራችንን ጭቃ እንዳይነካው "ከሚጨነቅ" ሆዳችንን ርሃብ እንዳይሞረሙረው አብስለን የምንመገብበት ውሃና መብራት ትኩረት እንዲያገኝ ቢያደርግልን የተሻለ ነበር፡፡ ጭቃውን በቦት ጫማ ስለምንወጣው፤ የዘንድሮው የኮብል ስቶን ሥራ በጀት ወደ መንገድ መብራት እንዲለወጥልን በዚህ አጋጣሚ እናመለክታለን - ክቡር ፕሬዝደንት!

ወደ ውሃ ጉዳይ እንለፍ፡፡ ከአዲስ አበባ ነዋሪ ግማሽ ያህሉ የውሃ ፍጆታውን የሚያገኘው በእኛው ቀበሌ ከሚመረተው ከለገዳዲ የውሃ ግድብ እንደሆነ መገመት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ውሃን በተመለከተ ለለገዳዲ ለገጣፎ ነዋሪ ከሞላ ጎደል የውሃ ቆጣሪ ገብቶልናል፡፡ ፈጣሪም መንግስትም ይመስገን! ውሃ የምናገኘው ግን በየአስራ አምስት ቀኑ አንድ ጊዜ ነው፡፡ በእኛው በራሳችን መንደር መንጭቶ በበራችን እየተንፎለፎለ በሚወርደው ውሃ ከእኛ ማዶ ያሉ ወገኖች

እንደልባቸው እየተጠቀሙ እኛ እንደ መብራት ሁሉ የበይ ተመልካች መሆናችን ሀዘናችንን መሪር አድርጎታል፡፡

ከጀሪካን የዘለለ የውሃ መያዣ ለሌለን ምስኪኖች የውሃ ቆጣሪ አስገብቶ ውሃን በአስራ አምስት ቀን አንድ ቀን መስጠት ሥጋ ሰጥቶ ቢላ መንሳት አይሆንም ክቡር ፕሬዝደንት? እዚያው ውሃው ዳር ስለሆናችሁ እንስራችሁን ይዛችሁ መቅዳት ትችላላችሁ በሚል ስሌት ይሆን ይህ ግፍ በእኛ ላይ የተጫነው?

የውሃ ልማት መስሪያ ቤት፤ የውሃ መስመሩን ከዘረጋ በኋላ የውሃ እጥረት አጋጥሞት ከሆነ፣ እንደ እኛ ላለ የውሃ መያዣ ታንከር መግዛት ለማይችል ህብረተሰብ ጥቂት የቦኖ ውሃ ማሰራጫዎችን በየአካባቢው ቢያቆምልን ምን አለበት? ክረምቱንስ ከቆርቆሮ ጣሪያ ላይ የሚወርደውን ውሃ ጭምር እያጠራቀምን ችግሩን አለፍነው፡፡ የበጋው ነገር ገና ከወዲሁ እያሳሰበን ስለሆነ ለመንግስታችን አቤት እንላለን፡፡

በመጨረሻ የማነሳው የትራንስፖርት ጉዳይ ነው፡፡ ክቡር ፕሬዝደንት! በሕገ-መንግስታችን አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት እንደ ለገጣፎ ያሉ በፊንፊኔ ዙሪያ ያሉ ከተሞች ከአዲስ አበባ የሚያገኙት የአገልግሎት ድጋፍ እንደሚኖርና ይህም በህግ እንደሚደነገግ ተቀምጧል፡፡ በዚሁ መሰረት፣ እዚሁ አጠገባችን አያት አደባባይ የደረሰው የአዲስ አበባ ከተማ ባቡር አገልግሎት ወደ ለገጣፎ እንዲሻገርና እኛም ተጠቃሚ እንድንሆን መጠየቅ ቅንጦት ስለሚሆን ለጊዜው እሱ ይቅርና ከአዲስ አበባ የሚነሱ የከተማ አውቶቡሶች ቁጥር ይጨምርልን፡፡ በተለምዶ "ሐይገር" የሚባሉት መካከለኛ አውቶቡሶች ይመደቡልን፡፡ የታክሲዎች አገልግሎት ተጠናክሮ ይቀጥልልን የሚለውም መልእክት ለአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን ይነገርልን፡፡

በአጠቃላይ፤ የእኛ ነገር ከሌሎች አካባቢዎች ጋር ሲነጻጸር "እናቱ የሞተችበት እና ገበያ የሄደችበት እኩል ያለቅሳል" እንዲሉ ነው ክቡር ፕሬዝደንት! እናም ለሁለቱ ምክር ቤቶች ባቀረቡት ንግግርዎ ላይ "የመብራት መቆራረጥን በተመለከተ መላውን ሕዝብ ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡ <u>**በተለይም የለገዳዲ-ለገጣፎ ነዋሪዎችን**</u>…" የሚል የማሻሻያ ሞሽን እንዳላቀርብ (በነገራችን ላይ ሕዝብም ሞሽን የማቅረብ መብት እንዳለው የምክር ቤቱ ደንብ እድል ይሰጣል) አሁን ጊዜው አለፈ፡፡ ብቻ ችግራችን በዚህ መልኩ እንዲታይልን ለመንግሥትዎ እናመለክታለን፡፡